# የሲ አይ ኤ ጠበል በአፍሪቃ ቀንድ! ግንቦት 7 እና ሻዕቢያ ጌታቸው ረዳ (የኢትዮጵያን ሰማይ ብሎግ አዘጋጅ)

May-5-2015

ወደ ርዐሴ ከመግባቴ በፊት፤ አንድ ነገር የምለው አለኝ።ስለ ሊቢያና የመን ኢትየጵያዊያን ስደተኞች ጉዳይ።

በሊቢያና በየመን ላይ በሞት አፋፍ ላይ ላሉ ወገኖቻችን ፤ አገር ወዳዶች ተሰባስበን ያዘጋጀነው የፔቲሽን ደብዳቤ “የአቤቱታ ፊርማ” በብዛት ለማግኘት እንዲቻል ታስቦ፤ በየድረገፆቻቸው ልከን እንዲተባበሩ የጠየቅናቸው “ውጭ አገር ያሉ የተቃዋሚ ድረገፆች” (ከአንድ ድረገጽ በስተቀር ፡ አርግጥ አንዱ አንደኛውን ፐቲሺን ለጥፎ ሁለተኛው ላይ አልተባበረንም) እምቢታቸው ያሳዩ ድረገፆች ለእምቢተኛነታቸው ምክንያት መልስ እንዲሰጡን ጠይቀናቸዋል። መልስ ከነፈጉን ግን የተቻለን ሁሉ ሞክረናልና አማራጭ ስለማይኖረን፤ ከነስማቸው/ፎቶግራፋቸው እና ዌብሳይታቸው ጭምር የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲያውቀው ለታሪክ እንዲመዘገብ ያመች ዘንድ ‘ልዩ ትችት” በሚቀጥለው ሰሞን ይቀርባል” ተከታተሉ። የፖለቲካ ልዩነታችንና ጥላቻን ወደ ጎን አስቀምጠን “የሰው ሕይወት ለማዳን” ተባበሩን ብልን እምቢ ለሚሉ ፍጡራን፤ፍርዱ በጉሮሮአቸው ቢላዋ ለተጋደመባቸው ሰዎችና ቤተሰቦቻቸው እንተወዋለን።

*አሁን ወደ ዋናው ጽሑፌ ይዤአችሁ ልግባ።*

ባንድ ወቅት መለስ ዜናዊ በቀየሰው፤ ጠባብ ብሔረተኞችና ጸረ አማራ፤ ጸረ ኢትዮጵያና ጸረ ሰንደቃላማችን ስብስቦች በገነባው በወያኔ ፓርላማ አዳራሹ ውስጥ አንድ ነገር ብሎ ነበር።

*"ግሎባላይዘሸን አዲስ ሃይል ነው። በሕሊና አስተሳሰብ ትግል የሚገፋ ሃይል አይደለም። "ፊዚካል" ሃይል ነው! ተራራ ያህል የቆመ ሃይል ነው። አንግፋው እንኳ ብንል፤ የማይቻል ሃይል ነው። ወደድንም ጠላንም ዓለም በዛው ሕግ እየተገዛ ስለሆነ፤ እኛም አማራጭ የለንም፡ ስለሆነም መግባት አለብን። ስንገባ ግን አንዱ እግራችን ጉድጓዱ ውስጥ አንዱ ደግሞ አፋፉ ላይ በመርገጥ ሳይሆን፤ ሁለቱ እግሮቻችን ሙሉ በሙሉ ጉድጓዱ ውስጥ ማስገባት ይኖርብናል....።" ብሎ ነበር።* ባጭሩ፤ ሲአይኤ ያቀደልንን ፖለቲካ እና፤ ገንዘብ የሚያበድሩን 'ዓለም አቀፍ ባንኮች' እንዲሁም፤ቅባት፤ዱቄትና ወተት..የሚለግሱን በጎ አድራጊ ድርጅቶች (ኤን ጆ ኦ)፤ በዘረጉልን መንገድ ካልተጓዝን፤ ስንዴም፤ቅባትም አናገኝም። በባሰ መልኩ፤ 'ሥለጣን ላይ መቆይት አንችልም' ማለቱ ነበር።

ይህ አባባል፤ እውነትነት አለው። እውነትነቱ ደግሞ፤ 'ሥልጣን ላይ የተቀመጡ የአፍሪቃ ወመኔዎች፤ዙፋናቸው ላይ

ተደላድለው መቀመጥ የሚችሉት፤ ግሎባላይዘሽን(ዓለም አቀፋዊነት) "በንግድ ልውውጥ፤ በሥልጣኔ ቅብብሎሽ እና በህበረተሰብ ውህደት" ስም ፤መዘውሩን የተቆጣጠረው 'ሃያሉ አሜሪካ እና የባንክ ባለሃብቶቹ፤እንዲሁም መሰል ሃያላን አገሮች' እስከፈቀዱ ድረስ እንደሆነ፤ እኛም ለ24 አመት የምናውቀው እውነታ ነው። አውነታነቱ የኺ ነው። መለስም ለተከታዮቹ ቁልጭ ባለ እውነታ የነገራቸው ይህንኑ እውነታ ነበር። ስለሆነም ነው  የወያኔ አወዳሽ የነበረቺው የ 'ቪኪ ሃደልሰን' መንትያ የምትመስለው "ወ/ሮ ስታርበሽን" (አጥንት ሲነጋገር)፤ እውነተኛ ስሟ፤ 'ዊንዲ ሸርማን' የተባለችው በአሜሪካ የውጭ መዋቅር ጽ/ቤት ውስጥ፤ በአፍሪቃ ነክ ከፍተኛ ባለስልጣን የሆነቺው ሴትዮ "በጫካ ሕግ የሚመራው ወመኔው የወያኔ መንግሥት" ስታሞግስ ለመስማት የበቃነውም ወያኔ በሁለት እግሩ ጉድጓድ ውስጥ ተምበርክኮ፤ የሚያዙትን ሁሉ ስለሚፈጽም ነው ።

ሥራዋ ፤የአፍሪቃ ወመኔዎችን መቆጣጠር ነው። ሁሉቱን እጋራቸው 'በተቆፈረላቸው ጉድጓዱ ውስጥ ማስገባታቸው ወይንም አለማስገባታቸው" መቃኘት ነው። ከጉድጓዱ ለመውጣት ሲቃጡ ግን፤ በጉድጓዱ ውስጥ ለማስገባት ፈቃደኛ የሆኑትን ተጠባባቂዎችን እንዲተኩ ለአለቆቿ መጠቆም ነው። ከእርሷ በፊት የነበሩት እነ ወ/ት ፍሬይዘር (የማውቀው አንድ ኤርታዊ ጸሐፊ 'በላይነሽ ዓጋመ' ይላታል)፤ ወ/ሮ ቪኪ ሃደልስተን፤ ሚሰተር ያማሜቶ፤ሄርመን ኮኸን፤

ሚቼ ፓል ኸንዝ እና መሰሎች.....ተልዕኮአቸው ‘ወመኔዎቹ” ሁለቱነም እግሮቻቸው በተዘጋጀላቸው ጉድጓድ ውስጥ ማስገባታቸወን መቆጣጠር ነው። ሙገሳውም፤ ማስፈራራቱንም፤የሚመነጨው ከዛው ቅየሳ በሚመጣ ግምገማ ነው።

እነዚህ ሁሉ የሲ አይ ኤ ጠበል ረጪዎች እና በየወሩ ወደ ስቴት ዴፓርትመንት ‘ምን እየተደረገ እንዳለ” በዘገባ የሚያስተላልፉበት ‘ኬብል” ምስጢራዊ መስመር አላቸው። ለዚህ ነው ወያኔ እያሞገሱ ‘ሽርተት ሲል ለማስፈራራት አንዲመቻቸው ደግሞ’ አዲስ አበባ ውስጥ ‘ቦምብ እያፈነዳ ያለው ‘እራሱ ወያኔ ነው’ እያሉ ያስተላልፋሉ። ሲያሰኛቸውም ኮንትራታቸው ሲያልቅ ለከፋ ቀን ፋይል መክሰሻና መክፈቻ አንዲያገለግላቸው “ሰብአዊ መብት ይጥሳል፤ ጋዜጠኛ ያስራል፤ ተቃወሚዎችን ያፍናል....ወዘተ” እያሉ በግልጽ ይዘግባሉ።

የዘገባውም ጠቀሜታ እጢያቸው ‘ዱብ” እስኪል በየወሩ፤ በየመንፈቁ ፤በየአመቱ፤ ያችን ማስፈራሪያ የሚዘግቧት ዘገባ እያስደነገጡ ባሉበት የአግልግሎት ጉድጓድ ሁለቱን እግሮቻቸው እንደገና እንዲያስገቡ ለማድረግ ነው። ሁሉም ባንድ የዕዝ ሰንሰልት የሚታዘዙ ናቸው (አሞጋሾቹም ነቃፊዎችም)።’ጠበል ረጪዎቹ’ በየአፍሪቃ አገሮች በተከፈተላቸው ጽ/ቤታቸው ሆነው፤ በወታደራዊው፤

በፖለቲካው፤ማህበራዊውና በምጣኔ ሃብቱ የእዝ ሰንሰለት የወጠኑትን ‘የአገር ቁፈራው’ መስመር በትክክል መከናወኑን አለመከናወኑ ይቆጣጠሩታል።መለስ ዜናዊ ስለ ግሎባላይዘሺን ሲያወራን የነበረው የተምበርካኪነት “ኑዛዜው” ትርጉም ይኼው ነበር።

እነ መለስ እና ኢሳያስ በእዛው ስር ተመልምለው ሥልጣን ላይ መቀመጣቸው በማስረጃ በፎቶ ኮፒ በቃለ መጠይቃቸው ሃቅ እንደነበር፤ ይፋ የሆነ መረጃ ካሁን በፊት እኔም ሆነ ሌሎች የዘገቡት ጉዳይ ነው። የአፍሪቃ ወመኔ መሪዎች አብዛኛዎቹ ሥልጣናቸው የተያያዘ ከሃያላኑ መንግሥታት ፈቃደኝነት የመነጨ ነው። አፍሪቃ ‘በእጅ አዙርም ሆነ በቀጥታ በውጭ ሃይሎች ዛሬም የተያዘች አህጉር ነች።

አገሮችን መቆጣጠር፤ በሁለተኛ ዓለም ጦርነት የጉልበት ትዕይንት (በተለይ በኢትዮጵያ ከጥንት ጀምሮ ማለትም ከ1909 ዓ.ም ጀምሮ የተከፈተው አምባሲ እስከዛሬ ድረስ) የዛሬ ልዩ የሚያደርገው ፤ ዓላማው አንድ ሆኖ ‘ስትራተጂው/ የጉዞው ስልት/ የሚጐነጐነው በግልጽ ሳይሆን፤ ‘በምስጢራዊ ብልሃት’ መሆኑ ብቻ ነው። ወመኔዎ መሪዎችን በሌሎች ወመኔዎች ለመተካት እንዲያመቻቸው የሚያዘጋጁ፤ መልማዮች፤ተመልማዮች እና የሚዘጋጅበት ቀጠናና ብልሃት ሌላ የቅየሳ ‘አውድ’ (መድረክ) አላቸው።

“በወመኔዎቹ ላይ የሚወያዩ “**እጩ ዲሞክራቶች**” ተቃዋሚዎችን መፈልፈል ነው። እነሱንም **እየዘለፉ** (ከረር ሲልም “አክራሪዎች፤ደርጎች....” እያሉ ፤ በሌላ በኩል ኮንግሬስ ፊትም ደጋፊና ሎቢ አዘጋጅተው ነፃ ንግግር’፤ ጩኸት እንዲያሰሙ እስከ መፍቀድ የሚዘረጋ ስልት አላቸው። መድረኩ የመጀመሪያው የብቃት መመዘኛ ማሳያ መድረክ ነው ማለት ነው። ተመልማዩ ፤የንግግር፤የማስረዳት፤ የድፍረት፤ የመልስ አሰጣጥ፤ ጭምትነቱንና አገርን ማስተዳዳር የሚችል መሆኑን፤ወይንም “እልከኛ አገር ወዳድ” ወይንም “ተምበርካኪ” መሆኑን አለመሆኑን የሚመዘንበት መድረክ ነው ማለት ነው። ለምልመላው አዲስ ከሆነ፤ ተመልማዩ ለዛው መድረክ የሚታጭ መሆኑን አለመሆኑን አያውቅም። ሗላ ነው በጠበሉ የሚረጨው።

ምልመላቸውን የሚያከናውኑት፤ በዚሁ መንገድ ነው። በመላ አፍሪቃ አብዛኛዎቹ ማለት ይቻላል ሥልጣን ላይ የተጎለቱ ጉልቶች፤ኮንግረስ ወለል ላይ ቀርቦ አቤቱታው እንዲያሰማ ይደረጋል። ጠበል ረጪዎቹ ዓይን ውስጥ ይገባል ማለት ነው (ወጣት ልጃገረዶች በአሸንዳ በዓላቸው ላይ ሲዘሉ፤ ቆሞ ቆነጃጅቶችን እያማተረ የሚያጭ ወንድ ‘ዓይኑን’ በቆንጆዎቹ እንደሚጥል ‘ጠባሸ’ ማለት ነው)። ከዛው ወደ ምልመላ ተቋም ትምህርት ቤቶች ይላካል (እንደ እነ ሻንግራይ/ዚምባቡዌ እና የኛዎችም ብዙዎቹ ማለት ነው ....!)።

ዶክተር ከተባለም ‘ዳክ’ ይባላል፤ ዶክተር ካልሆነም “ሪሰርቸር” ...ወዘተ..ይባላል።በልዩ ልዩ ተቋማት እየሰራ፤ ፖለቲካውን አንደ ጥጥ ፍሬ መዳመጥ ይጀምራል።የአፍሪቃ ነብስ አባት ይሆናል። በተለይ “አፍሪቃ ቀንድ” (ሆርን) የሚሉት ቀጠና ላይ በማተኮር ‘ቀንዱ’ ግሎባላይዘሽኑን እንዳይዋጋ ብዙ ‘አባት ነብሶች’ ከየመድረኩ እንደ አሸን ‘በራሳቸው ፍላጎትም ሆነ በሃያሉ መንግሥት ምልመላ” ወደ ሚዘጋጅላቸው “መድረክ” (ፎረም ይሉታል እነሱ) ብቅ ማለት ይጀምራሉ።

በ1993 ዓ.ም “ወያኔዎች አንዴት ገቡ?” ኮ/ል መንግሥቱስ እንዴት ተሰደዱ? የምዕራባዊያን ሚናስ? “ በሚል ርዕስ የጻፈው ወዳጄ “ይነጋል” አዲስ አበባ በብዙ መጽሔቶችና ጋዜጦች ያሳተመው ምስጢራዊ ሰነድ ትዝ ይላችኋል? አብሮ ከልጅነት ጅምሮ እስከ ሁለተኛ ደረጃ ድረስ አብሮት የተማረው የኣብዱል መሐመድ አባ ቦራ ታሪክ ትዝ ይላችኋል? የዛሬዎቹ እነ ግንቦት 7 እና ሻዕቢያ ወኪሎች እነ አስመሮም ለገሰ፤

*(እባካችሁ አትሳቁ። አስመሮም በየአመቱ ዜግነቱን እንደ ሞዴል ሸሚዝ ይቀያይራል። መጀመሪያ ኢትዮጵያዊ ነኝ አለን፤ ከዚያ አሜሪካዊ ነኝ አለ። አሜሪካዊ በመሆኑም ደስታውን ላሳስችል ብሎት በDecember 31/1988 ኒውዮርክ ታይምስ በተባለው ታዋቂ መጽሄት ላይ ጻረ ጥቁር የሆነው አረመኔው “ፕረዚዳንት ሬገን” ን ከእግር እስከ ራስ ጸጉሩ ድረስ እያወደሰ*

*ጻፈ። ትንሽ ቆየት ይልና ኤርትራ ነፃ ወጣች ሲሉት እየሮጠ ሄዶ 'ኤርትራዊ" ነኝ አለ። ከዚያ አስመራ ኢሳያስን እያቆላመጠ፤ ንግድ እያካሄደ፤ ትምህርት ቤት ከፈተ። አስመራ የከፈተው ት/ቤት ኤርትራዊያን እንግሊዝ የማስተማር ችሎታ የላቸውም (ደደቦች ናቸው ብሎ ነው መሰለኝ) ፤ከእንግሊዝ አገር የእንግሊዝ መምህራን ማፈላለግ ጀምረ። ኢሳያስ ከሥልጣን ሲወገድ፤ እንደገና የማን አገር ዜግነት እንደሚወስድ አንጠብቅ።....ታሪኩ ብዙ ነው፡...)*

እሱ እና እንዲሁም የጀግናው ዘርአይ ደረስ ቤተሰብ (ዘርአይ ደረስ፤ የአያቷ ወንድም ነው) የሆነቺው የሻዕቢያዋ አፈቀላጤ 'ሶፍያ ተስፋማርያም' (ኤርትራ ተቃዋሚዎቹ 'ሶፊያ አይዲድ፤ ጀነራል ሶፊያ፤ ባምቡላ፤ ጃርት ፤ ዊች ወዘተ...... በሚል ቅጽል ይጠሯታል) በማሰባሰብ "የአፍሪቃ ቀንድ ችግር መፍትሄ አፈላላጊዎች ተብለው ቀርበውላችኋል። **"Ethiopia and the Horn of Africa;** Conference on issues related to Ethiopia and the Horn of Africa Prospects for a

Stable. Democratic and Prosperous Future ”




በሚል ለሻዕቢያ ቱልቱላነት በሚሯሯጡት የግንቦት 7 ኢሳት ጋዜጠኞች/ሚዲያ በኩል የተዘረጋ ማስታወቂያ በመሪያቸው በግንቦት 7 መሪው በብርሃኑ ነጋ ደላላነት ይሄው በሚተባበሯቸው ሚዲያቸው ላይ ማስተወቂያ ለጥፈዋል።

እነ ‘አስመሮም እና እነ ሶፊያ’ የኢሳያስ አሽከሮች ‘ለኢትዮጵያና ለኬኒያ፤ለጅቡቲ፤ለሶማሊ፤ለኢትዮጵያ መፍትሄ ፈላጊዎች ሆነው ሲቀርቡላችሁ” አልገረማችሁም? የራሷን አርሮባት የሰው ታማስላለች ብለው ወላጆች የመሰሉት ምሳሌ ለዚህ ጉድ ጥሩ ምሳሌ ነው። በ“አብዱል መሐመድ አባ ቦራ” እግር የተተካ የሚመስል ሻዕቢያን ተሸክሞ ወደ አዲስ አበባ

ለማስገባት መከራውን እያየ ያለው ብርሃኑ የተናጋሪዎችን አመራረጥ አልገረማችሁም?

እስኪ ወደ አብዱል መሐመድ አባቦራ ንጽጽሩ እንዲመች ልመልሳችሁ። ይፋ የሆነው ወዳጄ ይነጋል በዘረጋው ሰነድ አብዱል መሐመድ አባቦራ 26 ምሁራኖችን መልምሎ (እነ እንድርያስ እሸቴን ፤ "ክፍሌ ወዳጆ"ን) እና በቅንጅት ጊዜ ፤ የቅንጅት አመራር ሆኖ፤ቅንጅት የተነጋገረውን ምስጢር በማስተላለፍ በወያኔ ቱልቱላ ጋዜጣ/መጽሄት እፍቲን (?) በማግስቱ እየታተመ ሲወጣ መረጃ አቀባይ በመባል ሲታማ የነበረው (ዛሬም አዲስ አበባ ውስጥ ተቃዋሚ ነው መሰለኝ) "ስሙን ረሳሁት" ዶ/ር......" የሚባለው እና ሌሎች እንደዚሁ አንዳንድ የውጭ ዜጎችን/ፈረንጆችንና አፍሪካኖችን በማስገባት "Inter African Group" የሚል ፎረም እያዘጋጀ በ1991 ለወያኔ 21 አሽከር ምሁራን መመልመሉን ይገልጻል።

ዛሬም በሚያስደንቅ እና በሚገርም ሁኔታ "የጅቡቲ፤የኬንያ፤ የሶማሊያ" ምሁራን በሌሉበት መድረክ ላይ "ምስኪኒቷ" ኢትዮጵያ በነዚህ ምሁራን ስትዳመጥ መዋሏ ነው። አብዱል ከአለቆቹ ከሲአይኤ የተሰጠው የቤት ሥራ ለማከናወን 'ከሻዕቢያ ጋር ሆኖ ከፍተኛ ወታደራዊ አዛዦቹን ምፅዋ ድረስ እየተነጋጋረ እንዲከዱና 'ኢትዮጵያ' በኃሳ እንድትከፋፈል ሲያደርግ" በተጠቀሰው መንገድ ፎረም እያዘጋጀ 'መንግስቱ ሃይለማርያምን መዳመጥ' አስመስሎ 'ኢትዮጵያን' እና ተሪኳን ሕዝቧን መዳመጥ ነበር። አሁንም እነ አስመሮም ለገሰ እነ

ሶፊያ (ይህንን ጽሁፍ ፈርተው ካልተውት) ኢትዮጵያን ‘ኮሎኒያሊት፤ኢምፔሪያል፤የብሔሮች-እስርቤት...’ ወዘተ....ወዘተ.....እያሉ ኢትዮጵያን የመዳመጥ ስልት ለመክፈት የተዘጋጀ መድረክ ካልሆነ፤ በአፍሪቃ ቀንድ የተገለለ፤ “ሽብር ፈጠሪና” ቀንደኛ “የግፍ ንጉሥ” የሆነው የኢሳያስ አፈወርቂ የሻዕቢያ ልውካንና አገልጋዮች፤ በዛ ቀጠና ኢሳያስን እንደ መፍትሄ ሰጪ አድርገው እንዴት አንደሚቀርቡት ለኔ ይገርመኛል። እርግጥ አገልጋይ ጌታውን መካብ የሚጠበቅ ነው። የብርሃኑና የኢሳት ተልዕኮም እነዚህን የአለቃቸው ወኪሎች ወደ ኢትዮጵያ ማሕበረሰብ በማምጣትና በማስተዋወቅ “የከፋ ቀን ወዳጃችን ሻዕቢያ” ነው፡ ብለው ለማስተዋወቅ እንደሆነ ሳይታለም የተፈታ ነው። ኢሳያስ



የራሱን ሕዝብ ማስተዳዳር አቅቶት እንደ “አ.ይ.ሲ.ስ” ኤርትራኖችን ምላሳቸው በቢላዋ የሚመትሩና የሚቆርጡ አሽከሮቹን እየሸለመ የሚውል ዕብድ “ስለ ምስራቅ አፍሪቃ ችግር” መፍትሄ አላቸው ብለው እነ ብርሃኑ ነጋ የኢሳያስ ተላላኪዎችን እነ ሶፍያ እና አስመሮም ለገሰን ጠጋግኖ ሕዝባችን እንዲቀበላቸው እያደረገው ያለው ደላላነቱ እጅግ አሳፋሪ ታሪክ ነው።

ጌታቸው በጋሻው "አነግ መገንጠልን ጠይቆ አያውቅም" ብሎ አንዳለ ሁሉ፤ ኢሳትን ብርሃኑም ስለ አለቃቸው ሻዕቢያ የሚሉን 'ሻዕቢያ/ኢሳያስ ስለ ኢትዮጵያ በጐ አሳቢ፤ ሁነኛ ወዳጅ ነው" የሚሉትን ፕሮፓጋንዳቸው እንደገና ለሕዝብ ማስደመጥ ነው። በእግረመንገዳቸውም የተሰጣቸው የቤት ሥራ በተግባር ለአለቃቸው ለኢሳያስ አፈወርቂ ለማሳየት ነው።

የሚያሳዝነው ግን ዛሬም ተመክሮ የማይሰማ ብዙ ደነዝ ሻዕቢያዎችን እና አሸከሮቻቸውን ለማድመት ዛሬም ጆሮው ለማድመጥ ጊዜው የሚያባክን ተስብሳቢ እንደሚኖር የታወቀ ነው።አሜሪካ ተቀምጠው "ኤርትራ" ያለውን "ሽምቅ ተዋጊ" እየመራን መቀሌ ደርሰናል ቢሉትም "ጭብጨባው የሚለግስ" ብዙ የዋህ አለ። ለነዚህም ይታዘናል።በባንዳዎች የሚታለል እና የተታለለ ብዙ ነው። ዛሬም ባይናችን እያየን ነው።

ስለ ባንዳዎች/የውስጥ አርበኞች 'በወዳጄ ይነጋል አገላለጽ ልጀምር። ይነጋል በዛው በ1993 አንዲህ ብሎ ነበር፡-

"ለሃገራችን ሠላምና አንድነት ስንሻና ተግባራዊም ለማድረግ ስንጥር ሙከራችን ሁሉ እንዳይሳካ የሚያደርገው ማነው? ምንስ ነበር ብለን ራሳችንን እንጠይቅና ከታሪክም አንደምንረዳው(ካልናቅነው በስተቀር) በጎ ጥረታችንን አንዳይሳካ የሚያደናቅፉን የውስጥ አርበኞች/ባንዳዎች ሆነው እናገኛቸዋለን..." ይላል።

እውነት ነው። አንዳንዶቹ እዚህ በማስታወቂያው ላይ ፎቶግራፋቸው ተለጥፎ የምናያቸው ሰዎች ‘በኢትዮጵያ ጠላትነታቸው መታወቂያ የያዙ፤የወጣላቸው ጸረ ኢትዮጵያ ደመኛሞቻችን ናቸው።” አንዳንዶቹም “ከብርሃኑ ነጋ ጀምሮ” ኢትዮጵያ ውስጥ ‘ዲሞክራሲ’ አስፍነን “እገነጠላለሁ ብሎ ለሚጠይቅ ድርጅት/ሕዝብ ‘ጥያቄው ለሚገነጥለው ሕዝብ አቅርቦ በድምፅ ብልጫ፤ የይሁንታ ደምፅ ካገኘ በጠመንጃ እንይዘውም ፤መገንጠል ይችላል። የዲሞክራሲ ትርጉሙ ይኼ ነው ብሎ የወያኔ አንቀጽ 39ኙን ዳግም  እውን ለማድረግ የተነሳ አደገኛ መሰሪና ቃሉ የሚምታታ ውዥምብራም ሰው ነው።

አንዳንዶቹም ‘ከብርሃኑ ነጋ ጋር በየአዳራሹ እየዞሩ “የአንድነት ሃይል” የሚባል ስምን የሚያንኳስሱ፤ ኦነግ የመገንጠል  ያቄ አቅርቦ አያወቅም፤ እያሉ ኦነጎች እንኳ ለማለት ብዙ ያልደፈሩትን ውሸት’፤ በይፋ ሕዝብ ፊት ቀርበው ሲዋሹ ‘ድምጻቸው በዩቱብ’ ተቀደቶ ለታሪክ ያስቀረጹ ፤ማፈሪያ’ ግለሰቦች ያሉበት ነው።

አንዳንዱም በሻዕቢያ የዕዝ ሰንሰለት/ወታደራዊ ኮማንድ/ የሚመራው “ለድምህት/”በግድ እንዲታገሉ ከታፈኑ የኦሮሞ ስደተኞች፤(ያለ ማስረጃ እንደማላቀርብ ታውቃላችሁ እና ይህንን ማስረጃ ላቅርብ) (Journey In The Dark Oromo’s Untold Story In Eritrea – See More At: [Http://Satenaw.Com/Journey-In-The-Dark-Oromos-Untold-Story-In-](Http://Satenaw.Com/Journey-In-The-Dark-Oromos-Untold-Story-In-)

Eritrea/#Sthash.IajY98mQ.Dpuf ( T.F/ AdamuNairobi Kenya
Source: SiiTube **Ethiopian News Oromo News)**

Nov 18th, 2014)ግማሽ ኤርትራ/ትግሬ የተወለዱ ትግሬዎች፤በተማረኩ በግዴታ የተመለመሉ ወታደሮች..ትግራይ ውስጥ ወንጀል ሰርተው ወደ ኤርትራ የሸሹ ትግሬዎች እና ከወያኔ ተማርረው ወደ ኤርትራ የሸሹ ትግሬዎች የተዋቀረው የሻዕቢያ "ብላክ ዋተር" (ቅጥረኛ-ቡድን) "ድምህት" እውነተኛ ኢትዮጵያዊ ነው እያሉ አድናቆታቸውን የቸሩ ሰዎች አሉበት።

"ድምህት" ለማታውቁ አገር ውስጥ ዘወትር ለምታነቡኝ አንባቢዎቼ ግራ እንዳይገባችሁ መረጃው ይኼው ላቅርብ፤ አንድ ፈረንሳዊ ጋዜጠኛ እና እንግሊዛዊው Martin Plaut ጋር ሆነው ፓሪስ ውስጥ አምና October 25 http://www.fithinews.com/index.php/2013-02-20-08-59-23/237-conversation-with-the-resistance ተመልከቱ።

አንዳንዶቹም 'እስላሙ 80 ከመቶ ነው ክርስትያኑ 20 ከመቶ ነው የሚለው ፕሮፓጋንዳ ለተከታዮቻቸው ሲሰብኩ የተደመጡ 'ከአገር ይልቅ እስልማዊ ሃይማኖትን የሚያስቀድሙ ናቸው። አገር እስላም ክርስትያን በፈጣሪ የማያምን ያቀፈ የሃይማኖቶች መፍለቂያ ነው። አገር ከሌለ

ሃይማኖት አይኖርም። አገር የማያስቀድም ሃይማኖት፤ስብእናን ይጻረራል። ነጣይ ነው። ወገንተኛ፤ቡድነተኛ ማለት ነው።

ምስኪኗ ኢትዮጵያም  በዚህ በግንቦት 7/ኢሳት "በአፍሪቃ ቀንድ" ኮንፈርነስ ላይ አዳራሽ ውስጥ አንደ ጥጥ ፍሬ ለመዳመጥ የተዘጋጁ የሻዕቢያ ባንዳዎች ብቻ እንዳይመስሏችሁ።




ምስኪን ዘፋኞችም ማሲንቆአቸው ይዘው **"ታሪክ ይፍረደኝ"** አንዳላሉ "**ታሪክ ባደፈረሱ  የባንዳዎች ባንዴራ ባሸበረቀ አዳራሽ ላይ**"  አንደገና ለመገኘት ፈቃደኞች የሆኑ ምስኪን ወንድሞቻችንም እንዳሉበት ሰምቻለሁ።ለወደፊቱ ዕጣ ፈንታቸው እና ዝናቸው ቢያስቡ መልካም ነው እላለሁ።

ሻዕቢያ ጋር ሆኖ የኢትኦጵያን ችግር ይፈታል ብለው የሚያታልሏችሁ ወይንም ከሻዕቢያኖች ጋር እስክስታ ስለተረገጠ፤ ችግሩ ይፈታል የምትሉ የዋሆች፤ እውነታው ልንገራችሁ። ኤርትራኖች ጋር አብረን ስለበላን ስለጠጣን እስክስታ ስለረገጥን (ያንኑም ቢሆን ያለ ማገም ምሁር/ ፎረም ጋባዥነት፡ ለ24 አመት ሕዝቡ መስተጋብሩን አላቋረጠም። ፖለቲካው ግን አልተፈታም።) ስለተሳሳቅን፤መጽሐፍ ቅዱስ/ቁርአን ስለደገምን ታምር ይመጣል የምትሉ እባካችሁ ጠለቅ ያለ ምርመራ አድርጉ። መነሻው እና መድረሻው እወቁበት። ችግሩ የሕዝብ ጠብ ወይንም ሰላም አይደለም። ችግሩ ፖለቲካ ነው።

ፖለቲካው ካልተፈታ ፤መብላት መሳቅ፤በደነስ፤መጋባት ችግሩ ሊፈታው አይችልም። ችግሩ ከመሳቅ ከመጠጣት ከመተሻሸት በላይ ነው። መሪዎች ፖለቲካው እንዳይፈታ ተብትበውታል። ሕብን የሚለያዩ እና ፖለቲካው የሚያዞሩት እነሱ ናቸው። እነሱ መወገድ አለባቸው። እነሱ እንዳይወገዱ ግን ሲአይኤዎች እና አሽከሮቻቸው፤ በኛ በኩልም በነ ብርሃኑ ነጋ በኩል “ዕርግብ” እያስመሰሉ ከሥልጣን እንዳይወርዱ ውዳሴ እያስሰሙ፤ መከራችንን እያራዘሙብን ይገኛሉ።

ወያኔ ተወግዶ፤ ሻዕቢያ በኢትዮጵያና በምስራቅ አፍሪቃ ሰላም ያመጣል የምትሉ፤ እባካችሁ “ከፖለቲካው ተገልላችሁ ጥሮታ ውጡ”! ሕዝብን የሚያራብሹት፤በፊትም አሁንም “ሁለቱ የስርዓቶቹ መሪዎች/ቡድኖች” እንጂ ሕዝብ ስላልሆነ በመጥፎ

መሪዎች ላይ ትኩረቱ፤ንግግሩ፤መድረኩ፤ትግሉ ሁሉ ካላተኮረ፤ "አንዱ ሰይጠን መሪ" እንደ መልኣክ "አንዱ ሰይጣን መሪ ደግሞ" "ሰይጣን" እያሉ፤ በአንዱ ሰይጣን ላይ ዓይንን ማትኮር፤ የሲአይኤዎች ስልት ነው። ልክ ሲአይኤ የባሰው የሳውዲውን ዲያብሎስ "መልአክ" አድርጎ የሊቢያው ጋዳፊን "ሰይጣን" ብሎ እየሰበኩ ያስወገዱትን አይነት ሴራ "ኢትዮጵያዊያን" መንቃት ይኖርብናል። እነ ብርሃኑ አሽከሮች ናቸው። ተልዕኮአቸውም በመጨረሻ የጠቀስኩት ስልት ነው።

ግንቦት 7 የተባለው ቅጥረኛ እና ጻረ ኢትዮጵያ ቡድን ቅንጅትን እንዳፈረሰው ሁሉ ዛሬም አገራችን ኢትዮጵያ በዲሞክራሲ ሽፋን ለመበተን ከአለቆቹ ያገኘውን ተልእኮ እውን ለማድረግ የሚያስታውሰን ነገር ቢኖር የአብዱል መሐመድ አባቦራ ሴራን ወደ ህሊናችን "ድቅን ይልብናል"።

አብዱል መሐመድ፤ ካሁን በፊት መለስና ኢሳያስን ወደ ዋሽንግተን ይዞአቸው መጥቶ ኢትዮጵያን ስይዙ የሚመሩበትን መንግሥታዊ አስተዳዳር ዝርዝር ከአሜሪካኖቹ ጋር ሲያስተዋወቃቸው "ኢንተር አፍሪካን ግሩፕ" በመጠቀም ነበር (ስለ አፍሪቃ ፤ስለ ሆርን የመፍትሄ ሃሳብና ምሁራን እነ እገሌ አሉ ኢያለ.....) ። ዛሬ ደግሞ የዚያ ቅጅ የሚመስል "ኢትዮጵያ ኢን ዘ ሆርን ኦፍ አፍሪካ" የሚሉ ሻዕቢያን ይዘውልን የመጡት ቡድኖች/ግለሰዎች ከሃያሉን መንግሥት ዘንድ ቀርበው ፕሮግራማቸውንና አጠናን የሚሉትን መፍቴሄ

ላመስተዋወቅ ወደ “እስቴት ዴፓርትሜነት” መርቷቸው የሚሄደው ማን ይሆን? ትንቢተ ምንምን......መርምሩ።

ወያኔም ሊኖርበት ይችላል። ያለ ምክንያት አንዳርጋቸውን ካዲስ አበባ በስልክ ልጆቹን እና ሚስቱን በስልክ እንዲነጋገር ሲፈቀድለት “ትንቢተ ምናምን የሚባለው .....መጽሐፍን መመርመር አለባችሁ። ሴቶች እህቶቻችን እራቆታቸው በወንድ ፖሊስ ምርማሪዎች ማላገጫ ሆነው ሲገረፉ፤ “አንዳርጋቸው ጽጌ” ካዲስ አበባ እስር ቤት እንዴት ለንደን ድረስ ስልክ እንዲደውል እንደፈቀዱለት ለራሴ መልስ አላገኘሁበትም? ይህ ልዩ ርህራሄ ከወያኔዎች በምን ታምር ሊከሰት ቻለ? “ትንቢተ ምናምን የሚለውን .....መጽሐፉን መመርምር አለባችሁ።

ከላይ ያነሳሁት ወዳጄ ይነጋል በላቸው፤በ1993 የነገረን ምስጢር አብዱል መሐመድ ፈሮም እያዘጋጀ የሚመለምላቸው ተናጋሪ ምሁራኖች መመዘኛዎች ነበሩት ይላል። ወያኔን ሕገ መንግሥቱንም ሆነ ፕሮፓጋንዳውና ዲፕሎማሲውን ለመርዳት ብቁነታቸውን ለማረጋጋጥ 7 መመዘኛዎች ነበሩት። አገር ለመሸጥ ዝግጁነታቸው ከገለጹ በሏላም “የሃገር መሸጫ ዋጋ” እያንዳንዱ ምሁር በሚፈልገው የውጭ ባንክ መነሻ በወር ከ3000 ዶላር በላይ ይከፈለዋል፥ የውሎ አበል (በቀን)፤ ከሚኖርበት ውጭ አገር ኢትዮጵያ ደርሶ መልስ በነፃ፤ በአገሪቱ የታወቁ ሆቴሎች ምግብ ፤መኝታ፤ መጠጥ በነፃ፤ትራንስፖርት እና ጥበቃ ይደረግለታል። ይላል።

አገር በመሸጥ በገቡት የምሁራኖቹ ቃል ፤ መጀመሪያ ንድፍና ድጋፍ እንደምሁራንነታቸው የሚሰጡት ትንተና እና ሙግት ድጋፍ መስጠት ያለባቸው ኤርትራን ማስገንጠል ነበር ይላል። ከሦስቱ ዋነኛው ሁለቱ ነጥቦች ስለ ኤርትራ የሚመለከቱ ዝርዝሮች እንደነበሩ ይገልጻል። ይህ ሁሉ ባየንበት 'እባብ' ፤ ዛሬ ደግሞ ሻዕቢያ ፤'ቀንድ ባወጣ የዘንዶነት' እድገት ላይ ሆኖ 'ምስራቅ አፍሪቃን' ባወከበትና ከዓለም ክብ ጠረጴዛ "ተገልሎ፤ዓይንህ ላፈር" በተባለበት ወቅት፤ ብርሃኑ ነጋ በደላላነቱ፤ከሰይጣንም ቢሆን (አይሲስም ሰይጣን ነው) እንሰራለን ባለበት እንደበቱና በራሱ ጋዜጠኞቹ በኩል ኢሳያስን ሲዘምሩለትና ሲቀድሱለት "ለገቡለት ውለታ" ስንት ያገኙ ይሆን?

"የሲ አይ ኤ ጠበል በአፍሪቃ ቀንድ! ግንቦት7 እና ሻዕቢያ" ክፍል 2 ይቀጥላል። ክፍል ሁለት የሚተቸው፤ የየግል አገራቸው ያለው ጉድና መከራ 24 አመት ሳይጠርጉ፤ ወደ ሰፊው ቀጣና ወደ ቀንድ አፍሪቃ ትችትና ንድፍ፤ጥናትና፤ ውይይት ማትኮር፤ 'የበከቱ' ምሁራን የመዝናኛ አውድማ መሆኑን እንመለከታለን (እኔ የምኖርበት አገር የባለ "ሦስት እግሮቹ" ድርሻና የሚረጩላቸው ጠበልም በሰፊው እንመለከተዋለን።)። ይቀጥላል........
አመሰግናለሁ ጌታቸው ረዳ getachre@aol.com